ስለ ፍቅር

ይህ ብዙ የሚወራለትና የሚባልለት ፍቅር፣ እያንዳንዱ ቅንጣት፣ በዚህ ዓለም ያለ እያንዳንዱ የፍቅር ዓይነት፣ በግጥም የሚገለጸው ፍቅር፣ በምርጥ ምርጥ ልብወለዶች የሚተረከ ፍቅር፣ በዘፈን የሚገለጽ ፍቅር፣ በፊልም ሊያሳዩት የቻሉትን ሁሉ የሚጥሩለት ፍቅር፣ እናት ለልጆቿ ያላት ፍቅር፣ ሴት ልጅ ለአባቷ የምታሳየው ፍቅር፣ ነፃ የሚያወጣ ፍቅር፣ ለባርነት የሚዳርግ ፍቅር፣ ያሳካኸው ፍቅር፣ ያጣኸው ፍቅር፣ የባከንክለት ፍቅር፣ የኖርክለት ፍቅር፣ እሞትለታለሁ ብለህ የተነሳህለት ፍቅር፣ ወንዶችን የሚያገዳድል ፍቅር፣ ሰይፎች የሚማዘዙለት ፍቅር፣ በአሳዛኝ ታሪክ የተሞላ ፍቅር ...

እነኚህ ሁሉ የፍቅር ዓይነቶች ናቸው። የሰው ልጅ የውስጥ ሀሳብ ነፀብራቆች። ስሜቶችና ፍላጎቶች።

ፍቅር ማስተጋባት ነው፣ ምንጩ ከአንድ ወገን በኩል የሆነ ማስተጋባት .. ከአንድ በኩል ወደ ሌላ አቅጣጫ የሚወረወር። አንተም፣ እኔም የምናውቀው ብቻችንን የተሸከምነው ፍቅር። ፍቅርን ማፍቀር ከመቻላችን በፊት እናውቀዋለን። ግና መውደድ ከመቻላችን በፊት ተወደን ነበር። ከመስጠታችን በፊት ተሠጥቶናል። ምን መስጠት እንዳለብን ሳንረዳ በፊት ተለግሰናል። ያ ፍቅር ልባችን የተፈጠረለት ፍቅር ነው። ሁሉንም ፍቅሮች የሚፈጥር እና የሚያስቀጥል ፍቅር እሱ ነው። ከሁሉ በፊት የነበረ፣ ከሁሉ በኋላ የሚቀር ፍቅር ነው።

ከሁሉ በፊት የነበረ፣ ጩኸቶች ሁሉ ካለፉም፤ ከሁሉ በኋላ የሚቀር ፍቅር ነው።

የአምላካችን የአላህ ፍቅር።

CamScanner

ዛሬ ስለሰላም ዱዓ አደረግኩ

ዛሬ ስለ ሰላም ዱዓ ሳረግ ራሴን አገኘሁት፤

ስለ ደህንነትና ፀጥታ ስለ ስከነት ሲጮህ ታዘብኩት::

ለብዙ ሺህ ጊዜያት ከአዕምሮዬ ርቁ ሄጃለሁ፤

አሁን ግና ዳግም ወደ አዕምሮዬም ተመልሻለሁ፤

ጌታዬ ሆይ!

እንደሰማኸኝ አስባለሁ፤

እንደተቀበልከኝ አያለሁ፤

በዚያ ባዶ ከፍል ውስጥ ብቻዬንማ አልነበርኩም፤

አንተ ከጎኔ የለህም ብዬ ከቶዉኑ አልጠረጠርኩም::

በዚያ አስጨናቂ ብቸኝነት፤

ብቻዬን አልነበርኩም በእውነት፤

በጉልበቴ ተንበርክኬ እጆቼን ዘርግቼ ለመንኩህ፤

በግንባሬም ተደፍቼ ተዋርጄ ተማፀንኩህ፤

ከዚያ በታች መዋደቅ ብችል፤

እምላለሁ ባደረግኩት ነበር::

ያ የስብራት ሁኔታዬ የዉስጤ ስሜት ማሳያ ነው፤

ካንተ ውጭ ረዳት እንደሌለኝ እውነተኛው መግለጫ ነው::

ያ ሁኔታዬን እኮ ካንተ ውጭ ማንም አያውቅም፤

በመገለል ያለን የሰው ልጅ ካንተ ዉጭ ማንም አይቀርብም::

የምትወድቅ አንዲት ቅጠልም ሆነ፣ የምትፈስ ዘለላ እንባ፤

የጨፈገገ ፊትም ይሁን ዉበ ደማቁ ፈገግታ፤

ካንተ ዕውቀት ውጭ አይደሉም፤

ከአይታህ አይደበቁም::

ዛሬም እንደገና አንድ ነገር ተማርኩ ...

በአጋጣሚ የሆነ ነገር አወቅኩ::

CamScanner

ይህች ዓለም የዕረፍት አገር አይደለችም፤

ታብረቀርቃለች እንጂ አታረካም አትሞላም።

በሷ ላይ ይበርድሃል፣ ትቸገረለህ፣ ይርበሃል፤

በሷ ላይ ትጨነቃለህ፣ ትደነግጣለህ፣ ታዝናለህ።

እሷ በርግጥ ትቀዘቅዛለች፤

አንዳንዴ ደግሞ እጅጉን ትቀዘቅዛለች።

ከምትወዳቸው ሰዎች ትለያለህ፤

ከሰው ተዋውቀህ ትርቃለህ።

በዚህም የተነሳ ትጎዳለህ።

ደስታና ሐዘን ወደ ሕይወትህ ሊገቡ ይሮጣሉ፤

ወደ ሜዳህ ገብተው ለመጫወት ተራቸውን ይጠባበቃሉ፤

ሁለቱም ባንተ ዉስጥ የተሻለ ቦታ ለመያዝ ይሽቀዳደማሉ።

የመሬት ስበቷ ጎትቶ ይጥልሃል፤

መሰበርና ደካማነት ደግሞ ያደማሃል፤

ማዘን ግድ ነውና ትካዜ ያንገላታሃል።

ግና

የዚህችን ዓለም ትክክለኛ ዋጋ በርግጠኝነት ልታውቅ ይገባል፤

ይህን ማወቁ ይጠቅምሃል፤ ግንዛቤን ይሠጥሃል፤

እንባዎች ከዐይንህ ቢወደቁም መውደቅ እንዳልነበረባቸው ያስታውሱሃል፣

መውደቅ ባልነበረባቸው ቦታ ነው የወደቁት።

መሆን ነበረበትን? ትላለህ ...

አንድ ዓለማዊ ጥቅም ሲያልፍህ ማልቀስ ነበረብህን?

ተገቢው ትክክለኛው እንባ ለጀነት አልነበረምን?

ለዚያ አላህ በሁለት መልኩ ደጋግሞ ለገለጸው ሥፍራ

'እዚያ ፍራቻም ሆነ ሐዘንም የለም" በማለት ...

ሥጋዬ ላይ ያለው ጠባሳ እሱን ያስታውሰኛል፤

CamScanner

ግራ እጄ ላይ ያለዉን የቃጠሎ ጠባሳ አብዝቼ የምወደው፤
ምን ያህል ደካማ እንደሆንኩኝ ስለሚያስታውሰኝ ነው፤
ሰው እንደሆንኩ ስለሚያስታውሰኝ እወደዋለሁ፤
ቃጠሎው፣ መድማቱ፤ መሰበሩ፣
ጠባሳውና መከራው ችግርና ሐዘኑ ሁሉ፤
ሁሉም የሚስታውሱኝ ነገር አለ::
እምን አሁን እኔ እሷ እዚህ ነኝ፣ እወድቃለሁ፣ አለቅሳለሁ::
እንደዚያው ሁሉ እንደኔው ሁሉ እሱም አጠገቤ አለ።
ከፍሌ ውስጥ አለ። ስላለም እንድተናነስ አደረገኝ።
ጌታዬ ሆይ!
አቅም እንደሌለኝ ማወቄና እንግልቴ መብዛቱ
እንደምታስፈልገኝ ይነግረኛል በየደቂቃ ሰዓቱ።
አንተው ጠብቀኝ ብዬ ተመፃንኩህ፤
እድትረዳኝ ለመንኩህ፤
በርግጥም ደረስከልኝ፤
ለዩኑስ፣ ለሙሳ እና ለእናቱ እንደደረስከው፤
ለኔም እንደዚያው ደረስከልኝ።
አንተ የሰላም ምንጭ ነህ፤
የብርታትም መንስኤ ነህ፤
በማዕበል መካከል መጠጊያ ነህ::
አዎ ....
ለዚህም ነው ዛሬ ለሰላም ስፀልይ ራሴን ያገኘሁት።

CamScanner

ከሕይወት ጋር ትግል

ዛሬ ስላንተ አሰብኩ

እነዚያን የነገርከኝን ቃላት አስታወስኩ

ፍጹም በሆነ መልኩ አሰብከኝ

የምትመታው ልቤን ፀጥ አሠኘህልኝ

ትንፋሼንም አስተካከልከልኝ፤

እነዚያን ቃላት ዛሬም ድረስ ተሸከሜያቸዋለሁ

እነሱ ከፍ አድርገውኛል፣ በፅናት ሞልተውኛል፣ ልብስ ሆነው ሸፍነዉኛል፣

ምክንያቱም ከሀመሙም በላይ ውስጤ አልቋል፤

ይህንን ታሪክ ለሺህ ዓመታት የኖርኩ ያህል ይሰማኛል፣

አሁን ለመተኛት ዝግጁ ነኝ፤

ለመተውም ዝግጁ ነኝ

ታሪኩ ያልቅ ዘንድ አሁን ዝግጁ ነኝ

ሰላምህን ለማጣጣም ዝግጁ ነኝ

ድምጽህን ለመስማት ዝግጁ ነኝ

ትከክል ነህ፣ አሸንፈሃል፣ አለውልሽ ... ስትለኝ

ግና የሚገርመው

ይህን ቦታ አውቀዋለሁ፤

ከዚህ በፊት እዚሁ ነበርኩ

አሁን ለመተኛት እየሄድኩ ነው፤

እባክህ አትጠይቀኝ

እባክህ አትጠይቀኝ

በቃ ልተኛ

ቃላትህ ከምላሴ ላይ ሳይጠፉ ልተኛ

“አንተ ሰው ሆይ! አንተ ጌታህን (በሞት) እስከምትገናኝ ድረስ ልፋትን ሰፊ ነህ፤ ተገናኚውም ነህ።” (አል-ኢንሺቃቅ :6)

CamScanner